ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org

በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
ሰኔ 13 ቀን 2009 ዓም የተላለፈ

# ከስቼ ቢያዩኝ ጅማት ለመኑኝ !

ጥንታዊትና ታሪካዊት ሀገር በመሆኗ ብቻ ፤ ያረጀች ያፈጀች ምድር ሆናለች ብለው የፈረጇት አጥፊዎቿ ፤ ከዓለም ካርታ ተሰርዛ- ተርስታ እንድትቀር የአቅማቸውን ሁሉ በማድረግ ላይ ናቸው። መሬቷን ብቻ ሳይሆን፤ ነዋሪዎቿም እንደ ዘር-ጨው ሟሙተው፤ ኢትዮጵያዊ ማንነታቸውም በሂደት እንዲጠፋ ማድረጋቸውን ቀጥለዋል ። ሀገራችን እዚህ አሳዛኝና አደገኛ ሁኔታ ላይ ልትደርስ የቻለችው፤ አይዞሽ አለሁልሽ የሚላት ሁነኛ ባለቤት በማጣቷ ብቻ ነው።

መክሳት - መመንመኗን፤ ማጣት - መደኅየቷን፤ መከፋት- መጎስቋሏን የተገነዘቡ ሁሉ፤ ጅማቷን ለመከፋፈል ይሯሯጣሉ። ጅማቷን ለመካፋል ከሚያደርጉት ሽሚያ ይልቅ፤ በጅማቷ ተሳስረው አንድ ቢሆኑ ኖሮ፤ የኢትዮጵያ ጅማት ልጆቿን አስተሳስሮ ፤ የማይበገር ኃይል ሆኖ ለመውጣት በእጅጉ ይረዳ ነበር። የኋላ ኋላ ይኸ መሆኑ ባይቀርም፤ ለጊዜው ግን በአስቸኳ አስተባባሪ ኃይልና የሚያስተሳስር ጅማት አልተገኘም ።

ዛሬ በሀገራችን ፖለቲካ አድማስ የሚጎሰመው ነጋሪት ፤ያስቸኳይ አድን ጥሪ ሳይሆን፤ የጥፋት አዋጅ ሆኖ ቀርቷል። የጥፋትና የሽብር ዐዋጅን ደምስሶ ፤ ያገር አድን አስቸኳይ ዕምቢልታ ማሰማት፤ ይዋል - ይድር የማይባል ሀገራዊ ጉዳይ መሆኑን ያልተገነዘበ ኢትዮጵያዊ አለ ለማለት ቢከድም፤ ድምፁ ግን የገደል ማሚቶ ከመሆን አልፎ፤ ሀገር አቅፍ አስተጋብኦ ሊያስገኝ አልቻለም ።

ከሠላማዊ ውቅያኖስ ዳርቻ ጀምሮ፤ እስከ አትላንቲክ ውቅያኖስ መዳረሻ ድርስ የሚከናወነው ስብሠባና ጉባዔ፤ ጥረቱ ቢያጓጓም፤ ወደ ተግባራዊ ምዕራፍ ሊሸጋገር ካልቻለ ፤ ያገራችንን የድረሱልኝ ጥሪ መመለስ አይችልም ። ስብሰባው፤ ምክክሩ፤ ውይይቱ፤ብሎም የስብሰባዎቹ ውሳኔዎች ቢታዎጁ ፤ ወደ ተግባር የሚተረጎሙበት ብልሃት ካልተገኘ፤ ከርሞ ጥጃ ከመሆን አያልፉም። ወደ ተግባር ለመለውጥ የሚያስችል አዲስ ምዕራፍ መከፈት የመጀመሪያው ርምጃ ሊሆን ይገባል። አግላይ ያልሆነና ሁሉንም ያካተታ መድረክ ወሳኝ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል ።ያለበለዚያ " ማንን ይዞ ጉዞ ? " የሚል ጥያቄ ሊያስነሳል ይችላል ። በየጊዜው ሊነሱ የሚችሉ አንኳር አንኳር ጥያቄዎች በሂደት ምላሽ እያገኙ እስካልሂዱ ድረስ ደግሞ፤ የሀገራችን ጉዳይ ፤ ስቆቃዊ ጮኸት ማሳማቱን ይቀጥላል። ኢትዮጵያም፤

ከሳሁ መነመንኩኝ ፤ ነጭ አጥንቴ ወጣ ፤ አፅሜ ብቻ ቀረ፤

አዳኝ መከታየ ፤ አለሁ ባይ ዜጋየ ፤ በመሥዋዕትነት ሰለተቀበረ ።

እያለች  መማመሏን ቀጥላለች። ላለፉት ግማሽ ምዕተ-ዓመት፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲያደርገው የቆየው ትግልና ሲያሰማው የነበረው የፍትኅህ  ጩኸት ውጤት አላስመዘገበለትም። እንዲያውም ፤ በተቃራኒው፤ አገራችን  የተሰጣት ምላሽ ፤በአስቸኳይ ዐዋጅ የጥፋቷ ፍጥነት እንዲፋጠን ማደርግ ሆኗል  ። በአንጻሩም፤ በተቃዋሚው  ጎራ ተሰልፋናል የሚሉት ሁሉ፤ ለአድኑኝ ምኅላዋ የሚሰጡት መልስ  አላገኙም። ተቸግረዋል። ተደናግጠዋል ።  በረባው ባረባውው ምክንያት ተበታትነዋል። የተደናገጠውን ጎራ የበለጠ እንዲተራመስ ለማድረግ አጥፊዎቿ  "  ሲሸበር ገዳይ "  እያሉ እንዲጨፍሩ ዕድል አግኝተዋል ። ጭፋራቸው ግን የአልሞት ባይ ተጋዳይነት መፍጨርጨር  እንደሆነ አልተገነዘቡትም።

በአሁኑ ወቅት፤ ከወያኔ በቀር፤፤ ሌላው ሁሉ ዐምኖ የተቀበለው አንድ ሀቅ አለ።  ይኸውም፤ ዛሬ በሀገራችን ሁለት ዐይነት ጦርነት እያተካሄደ ያለ መሆኑ ነው። ጦርነቱ የሚካሄደው  በመላው የኢትዮያ ህዝብና በወያኔ መካከል ነው።  በወያኔ በኩል፤ የሞት ሽረትና ህይወትን ለማትረፍ የሚደረግ የአልሞት -ባይ ትጋዳይነት፤ ሆኖ  "አልሞትኩም ብየ አልዋሽም "  የሚል ፤ በሥልጣን ለማቆየት የሚደርግ ራስን የመደልል መፍጨርጨር ነው።

በአንድ የታሪክ አጋጣሚ፤ ከኢትዮጵያ ወርቅ ማዕደን ላይ የተቀመጠ ቡድን ፤ ዐይኑ እያየ፤ ዦሮው እያሰማ፤ ወድዶ ሥልጣን በሠላም ይለቃል የሚል ብዥታን የኢትዮጵያ ሕዝብ ባላመስተናገዱ ምክንያት፤ ይኸው ዛሬ ሕዝባዊ ትግል ማድረጉን በየ አቅጣጫው  ቀጥሏል ። በመሆኑም፤ በኢትዮጵያ ሕዝብ  በኩል የሚደረገው የዐመፅ ጦርነት ኢትዮጵያን ከጥፋት የማዳን ፤ሀገራዊ ተልዕኮ ያለው ነው። ሕዝባዊ አመጽ በመሆኑ ግቡን ሳይመታ በቀላሉ አይበርድም። ዕሳት ቢዳፍን እንዳማይጠፋ ሁሉ፤ ሕዝባዊ ጦርነትም፤ የሀገርን ጠላት ሳያጠፋ በዋዛ በፈዛዛ አይበርድም  ። ይኸንን ሀቅ የማይገነዘቡ፤ የታሪክን ሀቅ መቀበል የማይደፍሩ ከንቱዎች ብቻ ናቸው።

በጨቋኝና በተጨቋኝ፤  መካከል የሚደርግ  ትግል፤ በሞት ሽረት ድባብ ውስጥ የሚገኝ ነው። አጥፊና ጠፊም በመሆኑ፤ አንዱ ሌላውን ሳያጥፋ በቀላሉ  የሚገላገል አይሆንም። ምናልባት ይኸንን አስከፊ ጥፋት ለማስወገድ የሚቻለው፤ የኃይል ሚዛኑ፤ በተወሰነ ሂደት ውስጥ፤  ጉልበቱ  ወደ አንዱ  ሳያጋድል፤ በአቻነት ደረጃ ሲከሰት ይሆናል ።  በዚህ ሁኔታ፤  ውጊያውንና ጠቡን  አስቁሞ፤ ወደ ሠላማዊ  ምዕራፍ ፤ ለመሸጋገር የሚቻለው፤  ከኅብረተሰቡ መካከል፤ ሚዛናዊና የማሳመን ችሎታ ያላቸው  ፤ የሀገር ወዳዶች/ አዛውንት ድምፃቸውን የማሰማት ዐቅም  አግኝተው የሕዝቡን ድምፅ ለማስተጋባት የሚያስችል ጉልበትና ተደማጭነት  ሲያገኙ ብቻ ነው። ይኸ ክስተት፤ በዘር ( አፓርታይድ) አገዛዝ ውስጥ የነበረውን የደቡብ አፍሪካን ችግር በዘለቄታ መልኩ ለውጦታል ።ሠላምና መረጋጋትንም አስፍኗል ። በኢትዮጵያም ፤ ይኸ የማይሆነበት ምክንያት አይኖርም።

 " ያገርን ሠርዶ  ለሀገር በሬ"  መመግብ እንጅ ፤  የሀገርን  ጉዳይ  ለባዕዳን አስልፎ ማስጠት ማለት ፤ " ለዕብድ ገላጋይ ድንጋይ ማቀበል  " መሆን ይሆናል።  ባዕዳን፤ ለኢትዮጵያ ሀገራዊ ጥቅም፤ ሠላምና ደኅንነት ማስብ ጉዳያቸው ስላይደለ፤ ጦርነቱም ሆነ ሠላሙ  በዕኛው በራሳችን እጅ ነው። ዕኛው ሳንስማማ እየቀረን ሁሉም ጉዳይ ከእጃችን እንዲያመልጥ አድርገን፤  ከተዝረከረክን፤ የምንይዘው የምንለቀው ከማጣት በስተቀር ፤ የፈየደ ጉዳይ ማስመዝገብ አንችልም። ሁሉም የበኩሉን ኃላፊነት ካልተወጣ፤ ነፃነት በውክልና አይገኝም ። ሁሉም  "ዕውነቱን እየተናገርኩ፤ ከመሸበት ማደር አለብኝ " ብሎ

ከወሰነ፤ ዛሬ በአብዛኛው ዘንድ መተማመን ጠፍቷል ። አንዱ ሌላውን ማመኑ ቀርቶ፤ የራሱን ጥላ እንኳ እየተጠራጠረ ካለበት ደረጃ ደርሷል ። ይኸንን ሁኔታ የሚከተተሉት የወያኔ መርጃ ሠራተኞች/ ሰላዮች ደግሞ ለራሳቸው ጥቅም በሚገባ ይጠቀሙበታል ። የኅብረተሰቡ እርስ በእርስ አለመተማመን፤ ለወያኔ ሥርግና ምላሽ ሆኖለታል ። መተማመን ስለተባለ ብቻ እርሱ ራሱ እንዲሁ አይመጠም። በመርኅ ላይ የተመሰረተ እያንዳኑ በጋሪዮሽ የሚመሰርተው ሁሉ - አቅፍ ተቋም (Institution ) ሲገነባ ፤ ሁሉ በጋራ የገነባውን ተቋም አምኖ ፤ አክብሮና ተማምኖ ሲሰራ ብቻ ይሆናል ።

ዛሬ አስተማማኝ ተቋማት አሉ ብሎ ለመናገር ከሚያስቸግርበት ሁኔታ ላይ ተደርሷል። በህዝብ ዘንድ አክብሮትና ተቃባይነት የነበራቸው ታሪካዊና ባኅላዊ ተቋማት ህያው ናቸው ብሎ ለማመን አስቸጋሪ ሆኗል ። በወቅቱ ያሉት የሃይማኖት መሪዎችም ቢሆኑ፤ በምዕመናኑ ዘንድ የቱን ያህል ተቀባይነት እንዳላቸው መስካሪው ራሱ ምዕመኑ ነው። ወያኔና ተባባሪዎቹ፤ የኅብረተሰቡን ኅብረ- ብኄራዊ ድርና ማግ (Fabric ) አመንምነውታል ። ይህ ማለት ግን፤ በአያሌ ዘመን የታሪክ ሂደት የተሳሰረ፤ የተጋመደና የተጥለፈለፈ ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ኢትዮጵያዊነት ይሸረሽረዋል ማለት አይደለም ። በሌላ አንፃር ሲታይ ግን፤ በዐለም ዙሪያ የነበሩ ሀገሮችና ህዝቦች ፤ በተለያዩ ምክንያቶችና አጋጣሚዎች እንዳልነበሩ ሆነው እንደቀጠሉ መገንዘብ ከተቻለ፤ ያ ዕጣ-ፋንታ፤ ሀገራችንን አይዳስሳትም ማለት እንዝኅላልነት ይሆናል ። ዳሰሰው ሳይነካት አልፏት እንዲሄድ መከላከል፤የኢትዮጵያን እንደ ሀገር መቀጠል የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ፤ ኃላፊነቱን የመወጣት ግዴታ ቆሞ ይጠብቀዋል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከረዥም ዘመን ሰቆቃ ካገኘው ተመክሮ በመነሳት ሁለት የተገነዘባቸው መሠረታዊ ጉዳዮችን ተረድቷል ። እነርሱም፡-

ሀ. ነፃነት ፤ ከጨቋኞች በበጎ ፈቃድ የማይገኝ መሆኑ፤

ለ. ነፃነት፤ ከጨቋኞቹ በግድ መነጠቅ ያለበት መሆኑ ነው።

እነኝኸን ሁለት መሠረታዊ ሀቆች ያልተረዳ አምባገነን ሥርዓት፤ አይከፉ አወዳደቅ ከመውደቅ በስተቀር ሌላ ምርጫ ሊኖረው አይችልም ።

የሕዝብ ትግል፡-

ሀ ምክንያቱ፤ ትክክል ከሆነ፤

ለ. መርኁ ንጽሁ ከሆነ፡

ሐ. ባህርዩ ተመስጋኝ ከሆነ የሚያጋጥመውን ማነኛውንም እንቅፋት ሁሉ ሊፈራ አይችልም።

ሁል ጊዜ በፍርሃትና ጭንቀት ድባብ ውስጥ የሚቁለጨለጨው ጨቋኝ እንጅ ተጨቋኝ ሊሆን አይችልም። ወያኔ የአገዛዝ ዕድሜው እያከተመ መምጣቱን አማካሪዎች ሳይነግሩት ራሱ አውቆታል ። በሁለት መሠረታዊ ምክንያቶች፡----

1ኛ.     የኢትዮጵያ ኅልውና ምሰሶ፤ ዋልታና ወጋግራ የሆኑት ሁለት ማኅበረሰቦች ፤ ኦሮሞና  ዐማራ ተባብረው አጋዛዙን ተቃውመው መነሳታቸው።   ይኸ በመሆኑ፤ ወያኔ ያገዛዝ አቅሙ  ተናግቶበታል። ወትሮውኑም ቢሆን ፤ "ኦሮሞና ዐማራ ከተባበረ ፤ መጥፊያ ነው ! " ብሎ ሲሰጋ የነበረው ፍርሃቱ ዕውን እየሆነ መምጣቱ ፤ የዘረኛ አገዛዝ ፍፃሜ መምጣቱን አውቆታል ። ወደደም ጠላ ትግድዶ እንደሚንበረከክ ተርድቶታል ።

2ኛ. ወጣቱ ትውልድ ፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ስሜት በልቡ ቅርጾ በመነሳት የድርሻውን ግዴታ እየተወጣ መምጣቱ ናቸው።

በመሆኑም፤ የኢትዮጵያን ጊዚያዊ መክሳት ዐይተው ፤ ጅማት የሚለምኗት ሁሉ፤ ትንሣዔዋን ዐይተው ነገ እንደሚያከብሯት አንጠራጠርም !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !